# ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌ ለሐቅ የቆሙ
# ውድ የኢትዮጵያ ጀግና ሰው ናቸው

ከሃቢሶ ገለታ

ከደርግ ጊዜ አንስቶ እስከ ዛሬዋ ስዓት እጅ ያልሰጡ ለኢትዮጵያና ለክርስትና እምነቷ በፅኑ የታገሉና የአካል መስዋዕትነት የኩፈሉ ጀግናና አንጋፋ ምሁር ናቸው ። ትናንት ደርግን በጠበንጃ የተታኮሱ ዛሬ ደግሞ ወያኔን ሳያሰልሱ ተደራጅተው በወንድነት ቆመው የሚታገሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚወዳቸውና የሚያከብራቸው ምርጥ ሰው ናቸው። የሚናገሩትና የሚጽፉት ሁልጊዜ ትክክልና ሐቅ ነው።

ቤተክርስቲያንን አስመልክቶ በቅርቡ የጻፉት ደግሞ ትክክልና እውነት ነው።ያብራሩት ግልጽ እንድሆንና እውነትን አውጥተው እናት ቤተክርስቲያን ለሁለት አልተከፈለችም ብለው አስተምረዋል። ይህ እውነት ነው አልተከፈለችም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሂዶ ቤተክክርቲያን አንድነቷ እንደተጠበቀ ነው። ዶ/ር ጌታቸው እንዳብራሩት እጠቅሰዋለሁ “ **ቤተክርስቲያን መከፈል የሚደርስባት በነገረ_መለኮት ላይ የተለያዩ ትርጉሞች ሲነሱና ስምምነት ሲጠፋ ነው**” በማለት የእኛ እናት ቤተክርስቲያን ይህ ያልደረሰባት መሆኑን አብራርተው ገልጸዋል። ይህ አልዋጥላቸው ያሉ ግለሰቦችና ክፍሎች በእውነቱ የወያኔ አፍቃሪዎች እንጂ የአገርና የሃይማኖት አፍቃሪዎች አይደሉም። ማንም ከእውነት የራቀ ነቀፌታ ቢጽፍና ዳንኪራ ቢረግጥ ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌ ያቀረቡትን ሐቅ አይለውጠውም።

ስለዚህ መነኩሴና ካህን በአበደና በአገመጠ፣ በከፈነ ቁጥር ልክ እምነትና ሃይማኖት እንደተከፈለና ምእመናን እንደተለያዩ አድርጐ ማቅረብ መሃይምነት ነው። ዶ/ር ጌታቸው እኮ የተማሩና በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ ብዙ የሚያውቁና የጻፉ፣ ያስተማሩና ያሳወቁ ሊቅ ናቸው። ሊቁ ቁጭ ብሎ ደቂቁን የምንሰማበት ምክንያት የለንም ። ሃቁ የዶ/ር ጌታቸው ነው።

የእኛ ሰዎች ችግር እውነትን አለመቀበል ነው። አወቅሁ ከማለት ደግሞ ማወቅ ይቀድማል ። በየት አገር ነው አንድ ፓይለት አይሮፕላኑ ችግር ሲያጋጥመው ተሳፋሪዎቹን ትቶ ራሱን ለማዳን እግሬ አውጭኝ ብሎ የሚሸሸው? አንድ የሃይማኖት መሪ ራሱን አይደለም ማስቀደም ያለበት።

ችግሩ የወደቀውና የተገፋው መላው ሕዝበ ክርስቲያን እንጂ አቡነ መርቆሬዎስ ብቻ አይደሉም። ታዳ ከመቸ ወዲህ ነው እነ አቡነ ጴጥሮስ እምቢ ለአገሬ፣ እምቢ ለሃይማኖቴ ብለው መስዋዕት ሆነው በሞቱበት አገር መነኩሴ ዓለምን አፍቅሮ ለነፍሱ መፍራት የጀመረው?? እስቲ አስቡት ፓትርያርኩ የመጣው ይምጣ ብለው እምቢ ቢሉ ምዕመናኑንና ካህናቱን፣ አገረን አልተውም ቢሉና ይህን አቋማቸውን ለሕዝበ ክርስቲያኑ ቢያሳውቁና ወያኔንም እንድሚገዝቱ ቢገልጽ የኢትዮጵያ ሕዝብ አቅፎና ደግፎ አይዛቸውም ነበር ? እሳቸው ተደፍረውና ተዋርደው ፣ በሐቅ ለነፍሳቸውና ለእግዚአብሔር የቆሙ ሌሎችንም በወያኔ እንዲረገጡና እንዲዋረዱ አደረጉ። እንዴ አቡነ ጴጥሮስ በቆራጥነት በክብር ቢሞቱ ኖሮ ቤተክርቲያናችን ተከብራ አንድነታችንም ይጠበቅ ነበር።እግዚአብሔርን የምናመልከው በእውነት አምነንና ተቀብለን ከሆነ ጠባቂያችንና አዳኛችን እሱ ስለሆነ የምንፈራውና የሚያስፈራን የለም። ይህን አባቶች ዘነጉት ?

ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ አበያተ ቤተክርስቲያኑን፣ አበያተ ገዳማትን፣ ሕዝብንና አገርን ያለ ጠባቂ ትተውና በትነው፤ ለወያኔ ጠባብ ዘረኛና አጋነንት አስተዳደር ጥለው ሲሰደዱ ስህተት አይደለም ? በዚያ የቀረው ካህናት፣ ሲኖዶስ፣መላ ክርስቲያን ሁሉ ጭቁን ነው፡ ወያኔንና አባ ገብረ መድህን ወዶ አልተቀበለም። ያ ጭቁን ነው። ካህናቱ ሁሉ አብሮ መሰደድ ነበረበት ይሆን ? እንደ ናንት እንደ ተችዎቹ ይመስላል።

ለመሆኑ የርቅና ሰላም እየተባለ የሚሽመገለውስ ለምን ነበር ? አንድ ሰው ቤቱን በወንበደና ቀማኛ ከነቤተሰቡ አስረክቦ ከሸሸ በኋላ በሽማግሌ በደባልነት ለመኖር ይደራደራል ወይስ ቤቱንና ቤተሰቡን ነፃ ያወጣል?

ወያኔ አባ ገብረ መድህንን ለፓትርያርክነት ለማስመረጥ በተጠራው የሲኖዶስ ጉባኤ ላይ ዛሬ ሕጋዊ ሲኖዶስን የመሰረቱት ጳጳሳት ለመወዳደር በጉባኤው ተካፍለዋል ለምን? ሥርዓተ_ ቀኖናው ሲኖዶስ መጣሱ ያን ጊዜ አልታወቃቸውም? ከዚያ በኃላ ወደ ውጭ በመውጣት አቡነ መርቆሬዎስን በመቀላቀል በውጭ በአሜሪካ ሕጋዊ ሲኖዶስን ለማቋቋም ተችሏል። ይህም ራሱን የቻለ ሌላ ስህተት ነው። እላይ እንደ ገለጽኩት መነኩሴ ዓለማዊ ሆኖ አገርና ሕዝበ ክርስቲያኑን፣ ካህናቱን ትቶ አይሰደድም፣ ሲኖዶስንም ከእናት ቤተክርሲቲያን ለይቶ በውጭ ሊቋቋም አይችልም። ይህ ከቀኖናው ውጭ ነው ። መለያየት እንጂ አንድነትንና ሰላምን አያመጣም።ስደተኛ ምእመናንንም ተከተሉን ማለት ደግሞ የተደጋገመ ስህተት ያደርገዋል።

ወያኔ ሲኖዶሱ በመጣስ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን እናወግዛለን፡ እንታገላለን።ጨቋኙ ወያኔና ሥርዓቱ ሁሉ እንዲደመሰስና ጭቁን ሲኖዶስ ሥርዓተ ተግባሩ እውን እንድሆን የእውነት አምላክ እንድረዳን አዘውትረን እንጸልያለን።የሁለቱም ሲኖዶስ ከእውነት የራቁ ስለሆነ አንዱ የሌላውን ስህተት እውነት አድርጐ ሲከተል ሌላውም በተመሳሳይ እውነትን ደብቆ ሰደተኛ ሁሉ እኛን ካልተከተልክ ገለልተኛ ወይንም መሀል ሰፋሪ ነህ ማለት በእውነት ቦታ የለውም ።

ሁለቱም ሲኖዶስ ከሥርዓተ_ቀኖናው ውጭ በመሆናቸው ለእውነት የቆምን ሁሉ አንከተላቸውም። የሚሄዱበት መንገድ ጠማማና ጐርባጣ በመሆኑ ቀጥተኛውንና ቀናውን ወደ እውነት የሚወስደውን በአምላካ እርዳታ እስከምናገኝ በጽናት እንቀጥላለን እንጂ ከዚህም ከዚያም ጋር አንቆምም ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ሁሉ ለእውነትና ለትክክለኛ ነገር በፅናት መቆም አለብን። እውነተኛና ለእውነት በቁርጥ በመፅናት ከአልቆምን ለሰላምና ደህንነት እንድሁም ለአንድነት ብቁ አንሆንም።እግዚአብሔርም የሚወደው አይመስለኝ። በአድርባይነትና በወገናዊነትም እምነትን ልናራምድና ክርስቲያን ሊያደርገን አይችልም።

የሰው ክብርን የሚነካ የተሳሳተንና አሉባልታን እንዳገኛችሁ መጻፍና መበተንን ብታቆሙ መጠነኛ ጨዋነት ይሆናል። ወደድህም ጠላህ ሐቁ ግን ዶ/ር ጌታቸው ኃይሌ የሚሉት ነው። እግዚአብሔር ከኛ ጋር ነው ።